# አብድዩ 1፡1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የነብዩ አብድዩ ትንቢት ያተኮረው በኤዶም ህዝብ ላይ ነው። እነዚህን ሁለት ክፍሎች ማለትም ዘፍ 25፡30ንና አብድዩ ቁ10ርን ስንመለከት መረዳት የምንችለው ኤዶም የይስሃቅ ልጅና የያዕቆብ ወንድም እንደነበረ ነው።
2. እነዚህ ሶስት ነገሮች "በአህዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለሁ" "እጅግ የተናቅህ ትሆናለህ" እና "እንደ ንስር መጥቀህ ብትወጣ፣ ጎጆህንም በከዋክብት መካከል ብታደርግ ከዚያ አወርድሃለሁ" የሚሉት ናቸው። እግዚአብሄር ይህንን የፍርድ ነገር በነዚህ ህዝቦች ላይ የተናገረበት ዋነኛውን ምክንያት በቁ3 ላይ እንደምናነበው ኤዶም ልቡ በትዕቢት ስለተነፋና ካለበት ሥፍራ ማንም ሊነቀንቀው እንደማይችል በነበረው አስተሳሰብ ምክንያት ነው።
3. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ከኤዶም ጥፋት ጋራ የሚያነጻጸራቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ሌባ ቤትን ሲዘርፍ የማይፈልጋቸውን አንዳንድ ነገሮች አስተርፎ እንደሚሄድና፤ ሁለተኛው ደግሞ ወይን ለቃሚዎች ወይኑን ሲለቅሙ ሁልጊዜ ቃርሚያን ሳይተው እንደማይቀሩ የሚናገሩት ናቸው። ከነዚህ ሁለት ሃሳቦች በመነሳት ነብዩ ስለ ኤዶም ጥፋት ሊናገር የፈለገው ዋና ሃሳብ፤ ሌቦቹም ሆኑ ወይን ለቃሚዎቹ የሚያስተርፉት የተወሰነ ነገር ይኖራል፤ ሆኖም ኤዶም ሲዘረፍ ግን ለእርሱ የሚቀርለት ምንም ነገር እንደማይኖርና የሸሸገው ነገር እንኳን ሳይቀር እንደሚረፍ ነው የሚነግረን።
4. እነዚህ ሶስት ዓይነት ሰዎች፤ የመጀመሪያዎቹ ወዳጆቹ ሲሆኑ የሚያደርጉትም ወደ ድንበር እንደሚገፉት ነው። ሁለተኛዎቹ ጓደኞቹ ሲሆኑ የሚያደርጉትም ነገር ያታልሉታል፣ ያሸንፉትማል። ሶስተኛዎቹ ደግሞ እንጀራውን የበሉ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህ የሚያደርጉት ደግሞ ወጥመድ ይዘረጉበታል። እግዚአብሄር የዚህ ዓይነቱን ፍርድ እንዲፈርድባት ምክንያት የሆነው ነገር በቁ10 ላይ እንደምናነበው ኤዶም ወይም ኤሳው በወንድሙ በያዕቆብ ላይ ካደረገው ግፍ የተነሳ መሆኑን እናያለን። ኤዶም በወንድሙ ላይ ግፍ ማድረግ የጀመረው ወንድሙን ያዕቆብን ማለፊያ ምንገድ በመከልከል ነው።
5. ቁ11ድን ስናይ ገለልተኛ ሆኖ መመልከቱ፤ ቁ12 ላይ ደግሞ በወንድሙ ስቃይ ኤዶም ደስ መሰኘቱ፤ በቁ13 ላይ ገለልተኝ ከመሆን፣ ሌሎች በሚያደርጉበት ነገር ደስተኛ ሆኖ ከመታየትም አልፎ እሱም ሃብቱን መዝረፍ እንደጀመረ፤ ቁ14 ደግሞ እሱም ወንድሙን ከማስጨነቅ አልፎ ከሌሎች ጋራ በመተባበር የያዕቆብን መከራ እንዳበዛ እናነባለን።
6. የእግዚአብሄር ፍርድ ቅንና ትክክል እንደሆን የሚያስረዳንን አባባል የምናገኘው በቁ15 ውስጥ ሲሆን "አንተ እንዳደረግኸው በአንተም ደግሞ ላይ ይደረግብሃል።" የሚለው ሃሳብ ነው። ይህንን ሃሳብ በአዲስ ኪዳን የምናገኘው በማቴ 7፡1-2 ጌታ በተናገረው ክፍል ውስጥ ነው።
7. ለያዕቆብ ነጻ መውጣት ይሆናል፤ ያዕቆብ ርስቱን ይወርሳል፤ የያዕቆብ ቤት እርሷ የተቀደሰች ትሆናለች። የነገር ሁሉ መደምደሚያ ይሆናል በማለት አብድዩ በተለይ በመጨረሻው ቁጥር ላይ ቁ21 የሚናገረው መንግሥት የተባለ ሁሉ የእግዚአብሄር እንደሆነ በማሳሰብ ነው ጽሑፉን የሚደመድመው።
8. በዚህ ክፍል ውስጥ የኤዶም ሃጥያት ሆኖ የተነገረው ሌሎች ያዕቆብን ሲያጠቁት እየተመለከተ በገለልተኛነት ወይም እኔን አይመለከተኝም የሚል ሁኔታ ምንም ነገር ሳያደርግ የመቅረት ሃጥያት ነው።